# ሴቷን ማን እንበላት?

ሳዳምጥ ሳስተውል ሳድግ በልጅነት፣
ጀግና በቤታችን በሰፈር ሲወለድ፣
በሴት ተመስሎ ይባል ነበር ወንዲት!

ተባእት እግሩ ዝሎ ሲነሳ ሲቀመጥ፣
እንስት ብርቱ ሆና ቀጥ ብላ ስትሄድ፣
ወንድ ቀሚስ ለበሰ "ወንዱ" እንዳንሰይማት፣
እስቲ ስም ፈልጉ ሴቷን ማን እንበላት?

ሁለት ጠጉር አብቅሎ ጭራ እሚያቀማጥል፣
ሻሹን ግጥም አርጎ የሚያሳልም መስቀል፣
ቆቡን ጥልቅ አርጎ "አባት ሆይ!" የሚባል፣
ቃሉ የእግዚአብሔር ቃል ሲሉ እሰማ ነበር።

አይነ-ጥላ ወግቶት ወይንም እርግማን፣
ቅስና ሲጠፋ ሽምግልናም ሲመክን፣
ጵጵስና ሲሞት አቡንም ሲዘብን፣
ቃሏን ስትጠብቅ ሰውታ ገላዋን፣
እስቲ መላ ምቱ ማን እንበላት ሴቷን?

ፍሬው ሁሉ ሾቆ አይጡ ትሉ በልቶት፣
መሳይ ተክል አጣን በደንብ የሚገልጣት።

የተማረች ጠቢብ ሊቅም እንዳንላት፣
ምሁሩ በዲግሪው ፍትፍቱን ዛቀበት።

ፍትህ ፈራጅ ሚዛን ዳኛም እንዳንላት፣
ዳኛው በመዶሻው ህይወትን ቀጨበት።

የሕግ አስከባሪ ጠበቃ እንዳንላት፣
አቃቢው በሕጉ ሕዝብ እግዚኦ አሰኘበት።

ወንድ ቀሚስ ለበሰ "ወንዱ" እንዳንሰይማት፣
ዳኛም ሰውን በላ "ክቡር ሆይ!" አንላት፣
ሽማግሌው ካደ በ"እርሳቸው" አንጠራት፣
መነኩሴው ዘበነ "አባ ሆይ" አንላት፣
ስጋዋን ለቃሏ ገብራ ስናያት፣
እንዲያው በፈጣሪ ሴቷን ማን እንበላት?

============//============


በላይነህ አባተ (abatebelai@yahoo.com)
ሰኔ ሁለት ቀን ሁለት ሺህ አንድ ዓ.ም.